# ባዮፕሲ
## Biopsy

ባዮፕሲ ማለት በጣም ቀላል ቀዶ ጥገና ሲሆን ቀዶ ጥገና ከተጠረጠረው የአካል ክፍል ብጣሽ ስጋ ቆርጦ ማውጣት ማለት ነው። ብዙ ዓይነት የጡት ባዮፕሲዎች አወሳሰድ አለ።



የመርፌ ባዮፕሲ፣ - በጣም ትንሽና ቀላል የባዮፕሲ አወሳሰድ ዘዴ ነው። ይህም ሐኪሙ በቢሮው ውስጥ በቀላሉ ሊያካሂደው ይችላል። ውጤቱም ከ 24-48 ሰዓት ውስጥ ማግኘት ይቻላል። በመርፌ ባዮፕሲ በጡት አካባቢ ያለውን ምርቁዝ ክፍል ጥቂቱን ሊቆርጥና ሊያወጣው ይችላል። የቀዶ ጥገናው፡- ኦንኮለጅስቱ/ራዲዮሎጂስቱ ሐኪም መሐሉ ክፍተት ያለውን ሰፋት ባለው መርፌ በመጠቀም ከታየው ምርቁዝ ክፍል ጥቂቱን ቆርጦ በማውጣት በአጉይ መነፀር ይመረምሩታል።

አንዳንዴ የምርቁዙን (lump) ቦታ በመርፌ መንካት ካልተቻለ በሜሞግራሙ ላይ ከታየ ባዮፕሴውን ለመውሰድ የተለየ አሰራር ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል። መሀሉ ስፊ በሆነ መርፌ ከምርቁዝ (lump) ውስጥ ጨቁኖ በመያዝ በሜሞግራም ወይም በአልትራሳውንድ ወይንም በ(MRI) በመረዳት የካንሰሩ እጢ የት እንዳለ ለማወቅ ይቻላል። የመርፌ ባዮፕሲ በሚደረግበት ጊዜ ሕዋሳትን በክፍቱ መርፌ እየተመጠጠ ይወሰዳሉ። ቀዶ ጥገናው እስከሚፈጸም መርፌው እንዳይዋዥቅ በመርፌው ጫፍ ላይ የሚንጠለጠል መንጠቆ ይታሰርበታል። የቀዶ ጥገናው ሐኪም መርፌውን ያስገባበት የተጠናወተውን አካባቢ ለመሆኑ በኤክስሬው ያረጋግጣል።

ባሁኑ ወቅት በአሰራር ላይ ያለው የኮር መርፌ ባዮፕሲ ነው። የኮር መርፌ ባዮፕሲ እንደመርፌ ባዮፕሲ አሰራሩ በጣም ቀላል በመሆኑ ሐኪሞች ቢሯቸው ውስጥ ሊያካሂዱት ይችላሉ። የምርመራውን ወጤት ከ24-48 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ማግኘት ይቻላል። የቀዶ ጥገናው ሐኪም፡- ኦንኮሎጂስቱ አሊያም ሬዲዎሎጂ በዚህ አሰራር በመጠቀም ብዙ ቅንጣቤ ከምርቁዙ (lump) ይወስዳል። የኮር መርፌ ባዮፕሲ የካንሰሩን ሐዋሳት እንዳሉ ከጤነኛው ሕዋሳት በተለይ ለይቶ ያሳያል።

ባዮፕሲው የተካሄደበትን ቦታ ምልክት ለማድረግ ትንሽ የብረት መቆንጠጫ ከጡት ውስጥ ይደረጋል። ባዮፕሲው ካንሰር እንዳለው ከታወቀ ተጨማሪ ቀዶ ጥገና ማድረግ ስለሚያስፈልግ የተደረገው የብረት መቆንጠጫ ለሐኪሙ ለተከታዩ ቀዶ ጥገና የካንሰሩ ቦታ አካባቢ በየትኛው የጡት አካባቢ እንደሆነ ለማወቅ ይረዳዋል።

የመርፌ ባዮፕሲና የኮር መርፌ ባዮፕሲ የካንሰር መራባት አደጋ አያስከትልም። መርፌው የካንሰሩን ሕዋሳት እንዳያሰራጭ የሚከላከል ሽፋን አለው። የዚህ አሰራር ዘዴ ምንም ችግር የማያመጣና ጥንቃቄ ያለበት በመሆኑ ካንሰሩን ለበትነው ወይም ሊያሰራጨው ወይም እንዲያድግ አያደርገውም። ነገር ግን የመርፌ ባዮፕሲ ወይም የኮር ባዮፕሲ የሚያስከትለው የአሰራር ችግር ካንሰር እያለ ካንሰር እንደሌለ አድርጎ የምርመራው ውጤት ማሳየቱ ነው። ይህ ሊሆን የሚችልበት ምናልባት መርፌው አብዛኛውን ጊዜ ያካንሰሩን ሕዋሳት ይዞ ሳያወጣ በመቅረቱ ሳይሆን አይቀርም።

ከውስጥ መቁረጥ ባዮፕሲ፣ ይህ እንደማንኛውም የቀዶ ጥገና የሚካሄድ የሕክምና ዘዴ ነው። በዚህ አሰራር ትንሽ ቲሹ ለምርመራ ከውስጥ ተቆጥቦ ይወጣል። ይህ ከውስጥ መቁረጥ ባዮፕሲ እንዲኖር የሚያስፈልገው ቀደም ሲል የመርፌው ባዮፕሲ ምርመራ ግልፅ የሆነ ውጤት ሳይሰጥ ሲቀር ወይም የካንሰሩን ምርቁዝ በጣም ትልቅ ሆኖ ሲገኝና በቀላሉ ለማውጣት አመቺ ለመሆኑ ነው። ይህ የውስጥ መቁረጥ ባዮፕሲ ካንሰሩ ቢኖርም ለመኖሩ አስተማማኝ ውጤት አይሰጥም።

በውጭ ቆርጦ የማውጣት ባዮፕሲ ወይም ላምፔክቶሚ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ አሰራር በካንሰርነት የተጠረጠረውን የጡቱ ምርቁዝ (lump) ባጠቃላይ ቆርጦ ለማውጣት የሚጠቀሙበት የሕክምና ዘዴ ነው። ይህ አሰራር ካንሰሩ ያለምንም ስህተት ለመወገዱና ላለመወገዱ ለመሰረታዊው ምርመራ አስተማማኝ ይሆናል።

ሁለቱም የመቁረጥና ቆርጦ የማውጣቱ ባዮፕሲዎች በክልኒኮች ውስጥ አለበለዚያም በሆስፒታል ወይም በሽተኛው ሆስፒታል ውስጥ ሳያድር ሊካሄድ ይችላል። ባዮፕሲ የተደረገውን የጡቱን ክፍል በመድሐኒት እንዲደነዝዝ ይደረጋል። ካንሰሩ በፊት ከነበረበት ደረጃ በበለጠ ተጠናክሮ 4ተኛ ደረጃ ከደረሰ በዚህን ወቅት ሐኪምሽ የኪሞቴራፒውን ሕክምና ውጤት ለማወቅ ብዙ የተለያዩ የሙከራ ምርመራዎች እንዲደረጉ ያዛል። እነዚህም የደም ምርመራ፣ የሽንት ምርመራ፣ ኤክስሬይ፣ አልትራሳውንድ ናቸው። አልትራሳውንድ፡- በድምፅ ግፊት የካንሰር እጢ የት እንዳለ ለማወቅ የሚደረግ የሙከራ ምርመራ ነው። የኢምአርአይ ስካን፡- ይህ ደግሞ በማግኔት ግፊት የውስጡን የሰውነት ክፍል ፎቶግራፍ በማንሳት የሚጠቀሙበት የምርመራ ዜዴ ነው። ሲቲ ስካን፡- ይህ ደግሞ በኤክስሬይ መልክ የኮምፒተር ጥበብ በመጠቀም የውስጡን ሰውነት ፎቶግራፍ ለማንሳት የሚጠቀሙበት የምርመራ ዘዴ ነው። የአጥንት ውስጥ ቅባት ባዮፕሲ(Bone marrow biopsies):- ይህም ጥቂት የአጥንት ውስጥ ቅባትን ለናሙና በማውጣት ምርመራ ማድረግ ነው። የአጥንት ውስጥ ቅባት ( marrow)፡- ማለት በአጥንት መሐል የሚገኝ ለሰውነት ደምን በመስራት የሚያገለግል የደም ምንጭ ነው።